EARLY STAGES

STRONG BEGINNINGS • BRIGHT FUTURES

# ተዘውትረው የሚነሱ ጥያቄዎች

www.earlystagesdc.org





## ኧርሊ ስቴጅስ (Early Stages) ምንድ ነው?

ኧርሊ ስቴጅስ፣ ዕድሚአቸው ከ 3 ዓመት እስከ 5 ዓመት ለሆናቸው ልጆች የሚያገለግል የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት የምርምራ (diagnostic) ማዕከል ነው። ልጅዎ ምናልባት ሊኖርበት ስለሚችል ማንኛውም ዐይነት ዝግመት (delay) ለማወቅ እርዳታ እናደርጋልን፤ ችግሩንም ለመቋቋም አገልግሎቶች እናዘጋጃለን። እነዚህ አገልግሎቶች ከገንዘብ ክፍያ ነጻ ሲሆኑ፣ ለዲሲ ነዋሪ ቤተሰቦች ሁሉ በነጻ የሚቀርቡ ናቸው።

በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለሚማር፤ ወይም ከቤት ትምህርት ለሚሰጠው፣ ወይንም ደግሞ ገና ከትምህርት ቤት ላልገባ ልጅ እና ለአንዳንድ  ቻርተር ትምህርት ቤቶች አገልግሎት እንሰጣለን። ልጅዎ ቻርተር ትምህርት ቤት የሚማር ከሆነ እባክዎን ስልክ ይደውሉልን። ማነጋገር የሚገባዎትን ትክክለኛ ሰው በመፈለግ ረገድ እንረዳዎታለን። በተጨማሪም፣ ልጅዎ በዲሲ የግል ትምህርት ቤት የሚማር ወይም በዲሲ የሕጻናት እንክብካቤ ማዕከል (DC Childcare Center)፣ ወይም ቅድመ ትምህርት መርሀ ግብር ውስጥ የሚሳተፍ ከሆነ፣ ምንም እንኳን ከዲሲ ክልል ውጪ የሚኖሩ ቢሆንም የልጅዎን ጉዳይ በተመለከተ ከእርስዎ ጋር አብረን እንሠራለን።

## መቼ ነው ለኧርሊ ስቴጅስ  ስልክ መደወል ያለብኝ?

ከ 3 ዓመት እስከ 5 ዓመት እድሜ ስለሞላው ልጅዎ የመዳበር እድገት ሁኔታ የሚያሳስብዎት ከሆነ፣ በመተማመን ያነጋግሩን። የተለመዱ አሳሳቢ ሁኔታዎች፣ አንድ ልጅ እንዴት እንደሚራመድ፣ እንዴት እንደሚናገር፣ እንዴት እንደሚጫወት፣ ወይም ምን ዐይነት ባህርይ እንዳለው፣ የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ያካትታል። ልጅዎ ተጨማሪ ግምገማ የሚያስፈልገው እንደሆነ ለመወሰን ሠራተኞቻችን ከእርስዎ ጋር በቅርብ ይሠራሉ።

## ኧርሊ ስቴጅስ ምን ምን ዐይነት አገልግሎቶች ያበረክታል?

ለ ኧርሊ ስቴጅስ የተመሩ ልጆች ሁሉ የእድገት መዳበር ማጣሪያ ይደረግላቸዋል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ አንድ ልጅ በጣም ጠለቅ ያለ ግምገማ እና በምርመራም ለተደረሰበት ዝግመት አገልግሎቶች እንዲያገኝ ይደረጋል። ኧርሊ ስቴጅስ፣ ልዩ የትምህርት አሰጣጥን፣ የንግግር/የቋንቋ፣ የአካል፣ የሙያዊ ሥራ ፈውሶችን (occupational therapy)፣ ሥነ ልቦናዊ አገልግሎቶችን እና የባህርይ ማሻሻያ ድጋፍ አገልግሎቶችን ለልጁ ሊያዝ ይችላል። ልጅዎ እነዚህ አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት ሆነው ከተገኙ ከክፍያ ነጻ በሆነ ሁኔታ እንዲሰጠው ይደረጋል።

## ልጄ ምዘና የሚያስፈልገው ከሆነ ምን ይደረጋል?

ቤተሰብዎ በመጀመሪያ ለቤተሰብ እንክብካቤ አስተባባሪ እንዲመደብ ይደረጋል። የዚህ አስተባባሪ ሰው ተግባር በሂደቱ ተግባር ውቅት በሙሉ እርስዎን መርዳት ነው። ስለሚካሄደው ተግባር ማናቸውንም ነገር ሁሉ እንዲረዱ ለማድረግ እና የሚኖርዎትን ማንኛውንም ጥያቄ ሁሉ ለመመለስ፣ ግምገማው ከመካሄዱ በፊት ያነጋግሩዎታል። የግምገማው ሂደት ተጠናቆ እስከ አበቃ ድረስ ቀጥታ ዝግጁ ሆነው በእጅ ስልክ ያገኟቸውል።

ጉብኝት በሚያደርጉብት በአንዱ ዕለት፣ ልጅዎ ከገምጋሚው ቡድን ጋር አብሮ ይሠራል። ቡድኑ ልጅዎን ለመገምገም በጨዋታ ክንዋኔዎች አቀራረብ ዘዴ ይጠቀማል። ልጅዎ እንዲዝናና እና የመረጋጋት ስሜት እንዲሰማው ለማድረግ ጊዜ የሚወስዱ ሲሆን፣  የግመማውን ሂደት በሙሉ መከታተል ይችላሉ።





## ለልጄ የሚሰጠውን የአገልግሎት ዐይነት የሚወስነው ማን ነው?

እርስዎ እና የግምገማው አባላት እንዲሁም የትምህርት አሰጣጡ ባለሙያዎች አንድ ላይ እንደ አንድ ቡድን ሁላችሁም በጋራ ሁሉንም ነገር ትወስናላችሁ። ይህ ቡድን፣ ለልጅዎ የሚያስፈልገውን የአገልግሎት ዐይነት እና አግልግሎቶቹንም የሚያገኝበት ትክክለኛውን የትምህርት ቤት ቦታ የሚወስነው ይኸው ቡድን ነው። የቤተሰብ እንክብካቤ አስተባባሪው (the Familiy Care Coordinator) አገልግሎቶቹ ሊሰጥባቸው ስለሚችሉ ትምህርት ቤቶች እና ክፍሎች እንዲያዩ እርዳታ በማድረግ ማናቸውም የተሞሉ ወረቀቶች ሁሉ ለትምህርት ቤት መድረሱን ያረጋግጣል።

## የኧርሊ ስቴጅስ ማዕከላት የት የት ይገኛሉ?

በ Walker Jones ትምህርት ምድረ ግቢ የሚካሄደው የ ኧርሊ ስቴጅስ ማዕከል፣ በ 1125 New Jersey Avenue NW ላይ ይገኛል። ቀድሞ ለመጣ ቅድሚያ በሚሰጥ የአመጣጥ ቅደም ተከተል መሠረት፣ ነጻ የመኪናዎች ማቆሚያ ቦታ ይኖራል። የአውቶቡስ ቁጥር 96 ማቆሚያ ልክ እዚያው ፊት ለፊቱ የሚገኝ ሲሆን፣ በጣም ቅርቡ የባቡር ማቆሚያ ጣቢያ፣ (Metro raile) ደግሞ red line (የቀዩ መስመር) ባቡር ጣቢያ ማቆሚያም ነው። የ green (የአረንጓዴው መስመር) እና የ yellow Line (የቢጫው መስመር) ባቡር ማቆሚያ በ Union Station እና Mt. Vernon Square 7th Street Conve -ntion Center ላይ ነው። የ Minnesoto Avenue የኧርሊ ስቴጅስ ማዕከል (በ 2011 በጋ የተከፈተው) በ 4058 Minnesoto Avenue NE, ከ Minnesoto Avenue በስተቀኝ በኩል በቀዩ የምድር ባቡር መስመር ጣቢያ ላይ የሚገኝ እና ይህም ለበርካታ የከተማ መጓጓዣ አውቶቡሶች መስመር መናኸሪያ ከሆነው ከ Orange Line (ከብርቱካናማው) መስመር ቀጥሎ ነው።

## አንድ ቤተሰብ የኧርሊ ስቴጅሰ ግልጋሎትን ለማግኘት ከየት ይጀምራል?

### እጅግ በጣም ጥሩው መንገድ ለእርስዎ ቀና የሆነው መንገድ ነው።

1. ማዕከሉን ቀጥታ ማነጋገር ይችላሉ።

2. ልጅዎን የሚያውቅ እና ስጋት ያደረበት ማንም ሰው (ለምሳሌ የልጁ ጠባቂ፣ መምህር፣ ሀኪም፣ ወይም የቤተሰብ አባል) ስጋቱን በመግለጽ ማዕከሉን ማነጋገር ይችላል። በዚህ ጊዜ ደግሞ እርስዎን እናነጋግርዎታለን። የጉዳዩም ሂደት የሚጀመረው ከእርሶ ፈቃድ ሲገኝ ብቻ ነው።

3. ልጅዎ ከወዲሁ በዲሲ ኧርሊ ኢንተርቬንሽን (DC Early Intervention Program) ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፍ የነበረ ከሆነ፣ የጉዳዩ አስተዳዳሪ ኃላፊ (the Case Manager) ካስፈለገ፣ ልጅዎን ለምርመራ ሊያስተላልፍ ይችላል።

## ማዕከሉን ለማነጋገር ዋነኛ ተመራጩ መንገድ የቱ ነው?

- በስልክ:- 202-698-8037
- በፋክስ:- 202-654-6079
- በኢ ሜይል:- referral@earlystagesdc.org
- በኦን ላይን ቅፅ:- www.earlystagesdc.org
- ወይም ወደ ማዕከሎቻችን በአካል ጎራ ብሎ ማነጋገር።

ለልጅዎ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነውን መንገድ እንደሚመርጡለት እናውቃለን፤ እኛም እንደዚሁ። በመሆኑም፣ ግባችን፣ ልጅዎ ትምህርት ቤት ገብቶ ለመማር እና ጥሩ ውጤት በማምጣት ትምህርቱ የተሳካለት እንዲሆን፣ ጠንካራ መሠረት ለመጣል በሚያደርጉት ጥረት እርስዎን መርዳት ነው።

EARLY STAGES
1125 New Jersey Avenue NW
Washington, DC 20001
phone: 202-698-8037
fax: 202-654-6079
DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS
Office of Specialized Instruction